OVERLAKE MEDICAL CENTER

OVERLAKE MEDICAL CLINICS

| | |
|---|---|
| **የስነስርአት ቁ.፡-** | **20245** |
| **ጽ/ቤት** | **(ክለሳ 3)** |
| **ዲፓርትመንት** | **የታካሚ የፋይናንስ አገልግሎት** |

# የግል ክፍያ ክትትል ፖሊሲ

## የግል ክፍያ አሰባሰብ ፖሊሲ እና ስነስርአት

**ፖሊሲ**

ቮርሌክ ሆስፒታል ሜዲካል ሴንተር (ኦኤችኤምሲ) እና ኦቨርሌክ ሜዲካል ክሊኒክ (ኦኤምሲ) ታካሚው በራሱ የሚከፍላቸውን መዋጮዎች መሰብሰብ ለሆስፒታሉ የጤና አገልግሎት ገቢ ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ በግሉ ክፍያ የሚፈጽም ታካሚ ሲሆን 100 በመቶ የክፍያ ግዴታ የታካሚው ይሆና፡፡ በተጨማሪም ኦኤችኤምሲ እና ኦኤምሲ የፋይናንስ ግዴታዎች በጤና አገልግሎት ሽፋን ውስጥ ሲሆን አሳሳቢ ሊሆኑ እንደሚችሉ እና የገንዘብ አሰባሰብ ፖሊሲውም ከዚህ ጋር እንዲሁም ከፋይናንስ ድጋፍ ፕሮግራም ጋር መጣጣም እንዳለበት ያምናል፡፡ ኦኤችኤምሲ እና ኦኤምሲ የዋስትና አከፋፈል መንገድን የሚጠቀሙ ሲሆን በዚህ አሰራርም የታካሚው ተጠያቂነት ለታካሚው ህክምና ወጪውን ከሚሸፍነው ሰው ጋር ተጣምሮ በጋራ ዋስትና ይጠየቃል፡፡ (ይህም ማለት ለሂሳቡ ክፍያ ዋስ የሚጠራበት አሰራር ነው) ይህ መዋቅር የተናጠል ክፍያ ጽ/ቤት (ኤስቢኦ) የሚባል ሲሆን የታካሚውን የክፍያ ሀላፊነት የሚመለከቱ ፖሊሲዎች ለኦኤችኤምሲ እና ኦኤምሲ በጋራ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ስነስርአት**

ታካሚውን የሚሸፍኑ የመድን ከፋዮች ክፍያውን ከፈጸሙ በኋላ ወይም ሀላፊነታቸው ካነሱ በኋላ የታካሚው ሀላፊነት ከፋዮቹ ቀደም ሲል ገብተውነት በነበረው መጠን ልክ ይዘዋወራል፡፡ ስለዚህም ታካሚው ከላይ በተመለከት ስነስርአት መሰረት ክፍያውን ይፈጽማል፡፡ ምንም አይነት መድን በሌለበት ሁኔታ ታካሚው በግሉ የሚከፍል ሲሆን አጠቃላዩ ተከፋይ ባላንስ የሚመለከተው የሂሳብ ክፍል በሚያወጣው ሂሳብ መሰረተ ይዘዋወራል፡፡

የታካሚው ባላንስ ከላይ በተመለከተው አግባብ ከተዘዋወረ በኋላ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን ጨምሮ መጠኑ 14.99 ዶላር እስከሚደርስ ድረስ በዋስትና ስር ይሸፈናል፡፡ (ለዋስትና ሽፋን አነስተኛ መጠን) ሲስተሙ ተገቢውን የሂሳብ መግለጫ አትሞ ያወጣል፡፡ የታተመው መግለጫ ታካሚው/ዋሱ የሚከፍሉበትን ቢል እንዲሁም ተከፋይ የተደረገበትን ሂሳቡ የሚያመላክት ይሆና፡፡ ታካሚው/ዋሱ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ በሌላ አሰራር ሙሉ ክፊያ ካልፈጸሙ (ከዚህ በታች በፋይናንስ ድጋፍ ፕሮግራም አርእስት ስር እንደቀረበው) ሲስተሙ የሚያወጣው መልክእክት ቁ. 1 ሲሆን በማስከተል የሚመጣው ቁ. 2 ይሆናል፡፡

ታካሚው ሙሉ ክፍያ ካልከፈለ ወይም በሲስተሙ ቁ. 2 መግለጫ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ለ7ላ የክፍያ ሲስተሙ መግለጫ ቁ. 3 አትሞ ያወጣል፡፡ የመጨረሻ መግጫ ታካሚው ሙሉ ክፍያ ላለመክፈሉ ገልጾ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ እንዲሁም ክፍያው ካልተፈጸመ ታካሚው በሪፈራል በከኦኤች ኤምሲ ወደ ሌላ ተቋም እንደሚተላለፍ ያስገነዝባል፡፡ ታካሚው ሙሉ ክፍያ ካልከፈለ ወይም በሲስተሙ ቁ. 3 መግለጫ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ለ7ላ የክፍያ ሲስተሙ መግለጫ ቁ. 4 አትሞ ያወጣል፡፡ ይህ መግለጫ ታካሚው በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ክፍያ እንዲከፍል ካልሆነም ወደውጪ ተቋም እንደሚላክ የሚያሳስብ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ታካሚው ማስጠንቀቂያዎቹ ተሰጥተውትም እርምጃ ካልወሰደ የታካሚው ሂሳብ የማይሰበሰብ እዳ በሚል ስር ተካቶ ወደ ሰብሳቢው ኤጀንሲ እንዲላክ ይደረጋል፡፡

ከዋሱ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ጥሪ የሚደረግላቸው የታካሚዎች ሂሳብ ተወካዮች ከዚህ በታች የተመለከቱትን የፋይናንስ ድጋፍ መንገዶች ተጠቅመው የደረሰው እዳ አከፋፈል በሚመለከት ለዋሶች ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

**የፋይናንስ ድጋፍ ፕሮግራሞች**

ኦኤችኤችሲ ታካሚዎች ለህክምናቸው የሚኖሩባቸውን የፋይናንስ ጫና ለማቅለል የተለያዩ የድጋፍ ፕሮግራሞችን ይሰጣል፡፡ የፋይናንስ አማካሪዎች እነኚህን ፕሮግራሞች በማስፈጸም ረገድ ሀላፊነት ያለባቸው ሲሆን በዚህም ታካሚው ሙሉውን

የህክምና ባላንስ እስኪከፍል ድረስ ተገቢውን ሁሉ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡  በበጎ አድራጎት/የማይከፈልበት እንክብካቤ ሲሆን ከ65 እስከ 100 በመቶ ድረስ የሚሆነው የታካሚ ክፍያ ሊተው ይችላ፡፡  የኦኤችኤምሲ የልገሳ ፕሮግራም ራሱን በቻለ ፖሊሲ እና ስነስርአት ተመልክቷል፡፡  ፕሮግራሞቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**ተገቢ ክፍያ ቅናሽ ፕሮግራም** ይህ ፕሮግራም ተፈጻሚ የሚሆነው ምንም አይነት የኢንሹራንስ ሽፋን በሌለበት ሁኔታ አፋጣኝ ህክምና ሲያስፈልግ ነው፡፡ (ፕሮግራሙ የሚመለከታቸው በህክምና መድን ፕሮግራም ለመታቀፍ ብቁ ሆነው ነገር ግን የተጠቃሚነት ገደባቸው የሚፈልጉትን ህክምና የማይሸፍን ለሆኑት ታካሚዎች ነው)  ታካሚው ከጠቅላላው የህክምና ክፍያ ላይ የ30 በመቶ ቅናሽ የሚደረግለት ሲሆን በአገልግሎቱ ጊዜ 50 በመቶ ቅድመ ክፍያ ለኦኤችኤምሲ ከፍሎ ቀሪውን 50 በመቶ ከተቋሙ ከወጣ በኋላ ባለው ጊዜ ይከፍላል፡፡  ታካሚው ለ30 በመቶ ቅናሽ ብቁ የሚሆነው ሙሉውን ክፍያ የመጀመሪያውን ክፍያ መከፈል ባለበት ቀን አጠቃሎ ከከፈለ በኋላ ይሆናል፡፡

**የታረዘመ ክፍያ እቅድ ፕሮግራም** ይህ ፕሮግራም ታካሚው የሚከፍለውን ድርሻ በሚመለከት ድጋፍ ለማድረግ የተቀረጸ ሲሆን ይህም የመድን ክፍያ በተከለፈበት እና የመድን አገልግሎት በሌለበት ሁኔታ በሁለቱም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የታካሚው ሂሳብ ተወካዮች የተራዘመ ክፍያ እቅድ ፕሮግራም ለመተግበር ከታካሚው ጋር አብሮ ይሰራሉ፡፡ ኦኤችኤምሲ ከዚህ የሚከተለው የክፍያ እቅድ መዋቅር አለው፡፡

| የሚከፈል መጠን | የሚከፈልባቸው ወራት |
|---|---|
| < $75 | 1 |
| $ 76 to $ 250 | 3 |
| $ 251 to $ 750 | 6 |
| $ 751 to $1,500 | 12 |
| $1,501 to $2,500 | 18 |
| > $2,500 | 25 |

የክፍያ አሰራር በቢዛ ከ25 ወራት በላይ መሆን የለበትም፡፡  ታካሚው በእነኚህ ሁኔታዎች ውስጥ መክል ካልቻለ ጊዜያዊ የክፍያ አሰራር ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ሊተገበር ይችላል፡፡  ጊዜያዊው አሰራር በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በተገለጹት አነስተኛ መስፈርቶች መሰረት መሆን አለበት፡፡ ይህም የመጀመሪያው ክፍያ እቅዱ ሲነደፍ ተከፋይ ይደረጋል፡፡

የታካሚው የሂሳብ ተወካዮች ይህንን እቅድ ለመጠቀም ለሚፈልጉ ታካሚዎች የሚሆን አስፈላጊ የጽሁፍ ስምምነቶችን እና የመልእክት ልውውጦችን ያደደርጋል፡፡   ታካሚው ክፍያ ካልፈጸመ የታካሚው ሂሳብ ተወካዮች ምክንያቱ እና መፍትሔውን ለመነጋገር ከታካሚው ጋር ይገናኛሉ፡፡  ክፍያን ለረጅም ጊዜ ማዘግየት ሂሳቡ የማይሰበሰብ እዳ ተብሎ እንዲያዝ ሊያስደሰርግ ይችላል፡፡

**የልገሳ እንክብካቤ/የፋይናንስ ድጋፍ፡፡** ይህ ፕሮግራም ታካሚው መክፈል የሚገባውን ድርሻ በመመልከት የመድን ክፍያ ከተከፈለ በኋላ ወይም ክፍያው በሌለበት ሁኔታ ለታካሚው የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ የተቀረጸ ነው፡፡ ታካሚው ወይም የታካሚው ሂሳብ ተወካዮች ለታካሚው የዚህን አገልገሎት መመዝገቢያ ቅጽ ሊልኩለት ይችላሉ፡፡  ታካሚው ወደ ሙሉ የማመልከቻ (የድጋፍ) ሰነዶችን ጨምሮ ደረጃው ሲደርስ የታካሚው ሂሳብ ተወካይ ማመልከቻውን ሙሉ ስለመሆኑ ይገመግማል፣ በልገሳ እንክብካቤ/የፋይናንስ ድጋፍ ፖሊሲ ላይ በተመለከተው መሰረትም የታካሚውን ገቢ ያሰላል፡፡  የታካሚው ሂሳብ ተወካዮች የልገሳ እንክብካቤ ቅጽ ለታካሚው የሚልኩበት ጊዜ የታካሚውን ሂሳብ በጊዜያዊነት እንዲቆም ማድረግ የሚኖርባቸው ሲሆን ይህም ታካሚው ከዚህ በላይ የተመለከቱትን የሂሳብ ማስጠንቀቂያ መልእክቶች እንዳይደርሱት ለማስቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የታካሚው ሂሳብ ተወካዮች ማመልከቻውን በሚከልሱበት ጊዜ ሀሳባቸውን (የሚቀነሰውን መጠን ጨምሮ) ለታካሚው ማሳወቅ አለባቸው፡፡  የታካሚው የፋይናንስ አገልግሎት ስራ አመራር በልገሳ እንክብካቤ ማስተካከያዎች ዙሪያ በሚደረጉ ውሳኔዎች እና ስሌቶች ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑ ሲሆን የተቀናሹ መቶኛ መጠንም በኦኤችኤምሲ ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡     ለልገሳ ቅናሽ ብቁ ያልሆኑ ታካሚዎች ለገቢ ክፍል ዳይሬክተር በተሰጠባቸው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል፡፡

**ተመላሽ ፖስታ እና ትክክለኛ ያልሆኑ የስልክ ቁጥሮች**

መልእክቶች ለኦኤችኤምሲ ከተመለሱ ትክክለኛ የፖስታ አድራሻ በመጠቀም በድጋሚ እንዲላኩ ጥረት ይደረጋል፡፡ የመጀመሪያው እርምጃ የታካሚውን ሂሳብ መረጃ ማረጋገጥ ሲሆን ይህም በኦኤችኤምሲ ዘንድ ታካሚው በሲስተም ውስጥ

ሌላ አድራሻ ያለው እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል፡፡ ይህ መረጃ ከሌለ ታካሚው በሰጣቸው ሁሉም የስልክ ቁጥሮች ትክክለኛ አድራሻ ተደውሎ ይጠየቃል፡፡ የተስተካከለ መረጃ ከተገኘ በኋላ የታካሚው የሂሳብ ተወካዮች ወይም የታካሚው የአገልግሎት ተቆጣጣሪ ስለ አከፋፈሉ እና ከታካሚው ጋር ስለሚደረጉ የመልእክት ለውውጦች የተስተካከለውን መረጃ ይጠቀማል፡፡ የተስተካከለ መረጃ ማግኘት ካልተቻለ የታካሚው ሂሳብ የማይሰበሰብ እዳ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ወደ ውጪ ኤጀንሲ ይተላለፋል፡፡

**ሂሳብን ወደ ቁጥጥር እና አሰባሰብ ማስተላለፍ የአሰባሰብ ኤጀንሲዎችን ስራ አፈጻጸም የሚመለከት ይሆናል፡፡**
ሁሉም አራቱም አይነት የክፍያ መግለጫዎች የተሰጠባቸውን ሂሳቦች ባለፉት 30 ቀናት ውስጥ ምንም እንቅስቃሴ ካልታየባቸው ለክትትል ወደ አሰባሰብ ኤጀንሲ ይተላለፋል፡፡ ሂሳቦች ወደ ኤጀንሲው የስራ ዝርዝር የሚገቡት በሲስተም ላይ ያለውን አሰራር ካለፉ በኋላ ነው፡፡ የገቢ ክፍል ዳይሬክተር ሳምንታዊ ስራዎችን ለማመቻቸት የሂሳቦቹን ቅደም ተከተል ያስተካክላል፡፡ የአሰባሰብ ኤጀንሲው የማጣሪያ ደረጃዎች በወርሃዊው የአፈጻጸም ጠቋሚ ሪፖርት ላይ ተመልክተዋል፡፡